<u>ፀረ አማራነት ማንንም ትግል ውድቅ የሚያደርግ ነው</u>

ወርቅ ትውልድ ነን ብለው በኩራትና በትዕቢት የሚቧርቁ ግብዞች አሉ ። ሰውን ከሰው በዘር ፣ በሀይማኖት፣ በፆታ መለያየት ህገወጥና ወንጀለኛነት ነው የተባለ ነው:: ወያኔ ግን ትግሬ ጀግና፣ ትግራይ ልዩ ምድር፣ ትግሬ ወርቅ ዜጋ ሲል የቆየ ነውና ከዚህ ዘረኛና አረሜኔ ቡድን ምንም ፀጋ አዘል ነገር ሊጠበቅ የሚችል አይደለም:: የአማራው ሕዝብ በተለይ በአስከፊ ጠላትነት ደረጃ ተመድቦ ለዓመታት ሲዘመትብት የቆየው በተለይ በነመለስና ስብሀት ነጋ ማለትም በወያኔዎች ጭፍን ፀረ አማራ ጥላቻ መሆኑ የሚታወቅ ነው::

በአማራ ሕዝብ ላይ ፀያፍ ዘመቻ ዛሬ ከየአቅጣጫው እየተካሄደ ነው:: አማራዎች በጅምላ ጨቋኝና አጥፊ ናቸው ብሎ የገንጣይ መንጋ ሲጮህ ዘመን አልፏል:: የትግራይ ጠባቦች በመስመራቸው ያላጀቧቸውን ትግራውያን የአማራ ኮራኩር ብለው ሲያንቋሽሹ ኦነጎች ደግሞ በኢትዮጵያ አንድነት የሚያምኑትን ኦሮሞዎች ዘመናዊ ነፍጠኞች ብለው ሲዘልፉ ከርመዋል:: ለነሱ ነፍጠኛን መምሰል አሳፋሪ ሆኖ ስለሚታያቸውም ነው:: የበደኖና የአሰሳን ሕዝብ ጨፍጫፊዎች ጀግኖች ሌሎች ቢሆኑ አያስደንቅም ለነገሩ:: በአማራ ሕዝብ ላይ ጥላቻን መሰረት አድርጎ የተካሄደው የጥላቻ ዘመቻ በአሁኑ ጊዜ በጣም ተባብሷል:: ወያኔ በትኩረት አማራን ማውገዝና ማንቋሸሽ ተልዕኮው ነውና ዛሬም “ ጭቁኖች” የሚላቸውን በዋና ደረጃ በአማራው ላይ ማስነሳትን ይጥራል:: አማራ እንደ ሕዝብ እስከዛሬ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ለተካሄደው ጭቆናና መከራ ሁሉ ተጠያቂ ተብሎ ሲወገዝ ቆይቷል:: ገዢዎች ሁሉ አማራ ተባሉ እንጂ ፖለቲካቸው ለሰፊው የአማራ ሕዝብ የፈየደው ብዙም አልነበረም:: ወያኔ መላ አማራው “ ተረፍ መረፍ ” ወይም ትርፍራፊ ከጭቆናውና ብዝበዛው አገኘ ቢል ም የትግራይ ሕዝብና ሌሎች ከነበራቸው ሁኔታ በባሰ የአማራው ሕዝብ መሰቃየቱ ሀቅ ነው: :

የአማራ ሕዝብ ወርቅ ነው መዳብ ባይባልም ( መባልንም አይፈልግም) ሰፊ ሕዝብ ነው:: በኢትዮጵያዊነቱ አምኖ ታሪክ የሰራም ሕዝብ ነው:: እነ ኢሳያስና መለስ ለኢትዮጵያ በመቆሙ በልዩ ልዩ መልክ ቢዘልፉትም አማራው ሕዝብ--እንደሌሎች ሁሉ--ለሀገሩ አንደነ ት ተቆርቋሪ ነው:: ጠባቦቹና ተገንጣዮቹ እንደሚሉት ግን ለሀገር አንድነት ተቆርቋሪ አማራ ው ብቻ አይደለም--ሚሊዮኖች ኢትዮጵያውያን ለሀገራቸው አንድነት እንደሚቆሙ ለሻዕቢ ያም ትምህርት ሰጥተዋል:: የወያኔ የታሪክ አዋቂዎችም አማራውን ሕዝብ ለመዝለፍና ጭቃ ለመቀባት መጣራቸውንም አንበናል ታዝበናል:: አተኩረን ስንመረምር የቀድሞቹም የዛሬዎ ቹም ፀረ አማራዎች ዋናው የሚያበግናቸው ጉዳይ በኢትዮጵያ አንድነት የሚያምኑ ኢትዮጵ ያውያን መኖራቸው ነው:: በየካቲት 66 ጊዜ ለምሳሌ ኢሕአፓ በተጨባጭ ህብረ ብሔራዊ

ድርጅት እንደነበር በመካድ ኢሕአፓ አማራ ትግሬ ነበር በሚል ሊወነጅሉት የሚጥሩ አሉ፡፡ አባ ኢትዮጵያ፤ አምሀራይ፤ ነፍጠኛ የሚሉትም ቅፅሎች ተለጥፈውበት ነበር ፡፡ አማራነት በራሱ ወንጀል ዓይነት ሆኖ ሲፈረጅ የቆየውን ዛሬም ይህንኑ በማስተጋባት ደረጃ ላቀዱት አሉታዊ ግብ ሁሉ ጋሬጣችን ይኸው ድርጅት ነው ብለው የሚቆጡ ጥቂት አይደሉም፡፡ የቀድሞ ነገስታት ጥፋት የተባሉ ሁሉ በአማራው ሕዝብ ላይ መጫናቸውን ታዝበናል፡፡ የወያኔ የታሪክ ተንታኝ ተብየዎችም ቢሆኑ ዛሬ የሚለፍፉት ታሪክ ሳይሆን የወያኔን የጥላቻ መርዝ ነው፡፡ ወያኔም፤ ኦነግም ሁሉም ተገንጣዮችም ቢሆኑ የጋራ ጥላቻን ይጋራሉ-- በአማራው ላይ፡፡

ይህ ዛሬ በልዩ ልዩ ክፍሎች የተከፈተው ፀረ አማራ ዘመቻ በመሰረቱና በይዘቱ ከዚህ በፊት ከታዘብነው የተለየ ባይሆንም ባዕዳን ዛሬም ሀገር ወዳድ የተባሉትን ሀይሎች ለማክሰም ባላቸው ዕቅድ የመጀመሪያ ቦታን የያዘ ነው፡፡ በበኩላቸው አማራው ትምክተኛ ኢትዮጵያዊ ነው ብለው የደመደሙ ናቸውና የአማራውን ቅስም መስበር ዋና ተግባር ነው ብለው ሲንቀሳቃሱ ዓመታት አልፈዋል፡፡ ዛሬም መለስን በሌላ ወያኔ ለመተካት ባላቸው ዕቅድ ሀገር ወዳድና የአንድነት ሀይል የተባሉትን ለማግለልና ለማክሰር መራወጣቸው ቀጣይ ሆኖ የሚታይ ነው ፡፡ የአንድነት ሀይሎች ቅስም ከተሰበረ የወያኔ አገዛዝ በአዲስ ተለጣፊዎች ታጅቦ ይቀጥላል ነው ዕቅዳቸውና እምነታቸው ፡፡ እንደ ጠባቦቹ ልፈፋ ከሆነ ከአማራው ውጭ ለኢትዮጵያ አንድነት የሚቆረቆር ሌላ ሕዝብ የለም ፡፡ ለአገዛዞች ጥፋትም ተጠያቂው የአማራው ሕዝብ በሞላ ነው ፡፡ ታሪክ ግን የሚያቀርበው ሀቅ የተለየ ነው፡፡ ብዙሃኑ አማራ በአገዛዞች የተበደለና የተሰቃየ እንጂ እነ ወያኔ እንደሚሉት ወይም ኦነግና ሻዕቢያ እንደሚያጮኹት ጭቆና ከተባለው ትርፍራፊ ውይም ጥቅም ያገኘ አልነበረም፡፡ የአማራው ሕዝብ ስቃይና መከራ ከትግራይና ኤርትራ በባሰ ነበር ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ የምጣዱ ሳለ የእንቅቡ ተንጣጣ ሆኖ እንጂ በበደል ሚዛንማ ተበደልን ብለው ኡኡ ካሉት በላይና በቅድሚያ ተጠቃሁ ባይ አማራው በሆነ ነበር፡፡

ፀረ አማራነት አያዋጣም አይጠቅምም ስንል ይህ ሕዝብ የተለየና ሁሉን ከሀሊ ነው ለማለት ሳይሆን ይህ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ሕዝብ ሰላማዊና ሁሉን አክባሪ ቢሆንም ሲጠቃ ደግሞ ቁጡ ነብር ነውና ሚዛኑና ክብደቱ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ ሕዝብን ማስቀየምና ማስቆጣት ሁሌም ቢሆን ጎጂና ጠቃሚ አይደለም፡፡ ብዙሃኑ የአማራ ሕዝብ በአንድነት ጥያቄ ላይ በማያወላዳ መልኩ ለሀገር አንድነት የቆመ ነው፡፡ ይህ ሐጢያት ወንጀል ተብሎበት ከተወገዘ ደግሞ ራሱን መከላከሉ የግድ ይሆንበታል፡፡ አማራን ያህል ሰፊ ሕዝብ አግልሎና አውግዞ የለውጥ ትግል አካሂዳለሁ ማለት ዘበት መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ ለስልጣን ባንበቃ ለዚያ የሚሮጡትን ማደናቀፍ እያቅተንም የተባለውን ያስታውሰናል፡፡ ዛሬ በየአቅጣጫው

በአማራው ላይ የተከፈተው ፀያፍ ዘመቻ በአጭር ካልተቀጨ ውጤቱ አሳዛኝ ይሆናል ፡፡ የአማራውን ሕዝብ በቀጣ በሌላ አቅጣጫ የሚሰድ ሊሆንም ይችላል፡፡ ፀረ አማራነት በመሰረቱ ፀረ ሕዝብነት ይሆናልና ለትግል በምንም ዓይነት ጠቃሚ አይደለም፡፡ ያዋጣል ብለው የፖለቲካ ክስረታቸውን የአማራውን ሕዝብ በማውገዝ ሊወጡ እየጣሩ ያሉት ክፍሎች መጨረሻቸው ባዶ መሆኑን ለማወቅ ትንቢተኛ አያሻም፡፡ ለዚህም ነው አማራውን ሕዝብ በኢትዮጵያዊነቱ አከብረን ይዘን ለጋራ ትግል ማሰለፍ እንጂ በማይጠቅምና በማያዋጣ ዘመቻ ሰለባ ለማድረግ መነሳቱ በጣም የተሳሳተና ጎጂ ስምሪት ነው፡፡ የአማራው ሕዝብ ለኢትዮጵያ አንድነት መሰዋቱ የሚከበርና የሚደነቅ ነው፡፡ ለኢትዮጵያ ስርየት አማራው ሕዝብ--እንደ ሌሎቹ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ-- መታገሉና መሰዋቱ ወሳኝ ነው፡፡

በጋራ ለሀገራችን እንታገል !